***አዲስና ማሻሻያ (Updated) Nov. 18, 2020***
*(Key changes marked by highlighted*

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS
Office of School Improvement and Supports

# የተማሪ ባሕሪ (Behavior) መረጃ ለቤተሰቦች: የትምህርት ዓመት 2020-21

## በመኖሪያ ቤት እና በትምህርት ቤት ውስጥ፣ አዎንታዊ የተማሪ ባሕሪ (Positive Student Behavior) እንዲኖር ማገዝ

DCPS ለእያንዳንዱ ተማሪ ዕድሎች የሚሰጥ እና መበልጸግ እንዲችሉ የሚያግዛቸውን አካባቢ (environment) ለመፍጠር ይጥራል። ለዚህ ትጋት አንዱ አካል እንዲሆን በማለት፣ ልጁን በሙሉነት የሚደግፍ እና እያንዳንዱ ተማሪ ደስተኛ እና ጥብቅ የሆነ የቀለም ትምህርት ተሞክሮዎች እንዳገኙ ለማረጋገጥ የተመቻቸ የመማሪያ አካባቢዎችን ለመፍጠር DCPS ይሠራል። ስኬትን ለማስፋፋት፣ የማህበራዊ ስሜታዊነትን ብቃቶችን የማሳደግ ጥረትን እንደግፋለን። በመኖሪያ ቤት ለሚማሩ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች፤ ከDCMR የቻፕተር (Chapter) 25 እና የተማሪ ወደትምህርት ቤቶች ተገቢ በሆነ ሁኔት ማግኘት ድንጋጌ (Student Fair Access to Schools Act) ጋር ጎን ለጎን የሚሄደውን፤ የተማሪዎች ስነስርዓትን ከታማኝነት ጋር፤ መመልከትን DCPS ይቀጥላል። ምርምር (Research) እንደሚነግረን ከሆነ፣ ተማሪዎች በተለይ ከአስተማሪያቸው(ዎቻቸው) ጋር በትምህርት ቤቶቻቸው ውስጥ ከአዋቂዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነቶች ሲኖራቸው፤ ለሚጠበቁባቸው ነገሮች በበለጠ አዎንታዊነት ምላሽ ይሰጣሉ።

በመኖሪያ ቤት ውስጥ መማርም ሆነ በትምህርት ቤት፣ DCPS በስሜት ቀውስ-ምላሽ አሰጣጥ ሌንስ (trauma-responsive lens) አማካኝነት ተማሪዎችን ይረዳል። አስተማሪዎች፣ በስሜት ቀውስ-ምላሽ ሰጭ (trauma-responsive) የሆነ የመማሪያ አካባቢ ውስጥ እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ የተካተቱት ምሳሌዎች፡ አስተማሪዎች አዎንታዊ እና የማረጋገጫ አነጋገሮችን በየዕለቱ መጠቀም፣ ራስን ለመቆጣጠር (self-management) የሚያግዙ ምንጮችን (resources) ማቅረብ፣ በግንኙነት ላይ ዕምነትን መገንባት እንዲችሉ ጊዜ መስጠት፣ እና የማስተማር፣ ሞዴል የማድረግና የትምህርት ቤት አቀፍ ባሕሪ (school-wide behavior) የሚጠበቁትን እንደገና ማጠናከር ናቸው። ክፍል (Section) A፤ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ብቻ ለሚማሩ፣ መረጃዎችን ያካትታል። ክፍል (Section) B፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ ለሚማሩ፣ (ለ 'CARE' ክፍሎች እና ለሁሉም በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ክፍለጊዜዎች) መረጃዎችን ያካትታል። ክፍል (Section) C፤ በሁሉም ዓይነት አቀማመጥ ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ መረጃዎችን ያካትታል።

## A. ከመኖሪያ ቤት መማር

*ይህ፣ በመኖሪያ ቤት ውስጥም ሆነ በCARE ክፍል ውስጥ፣ በምናባዊ (virtual) መማር የሚሳተፉ ሁሉንም ተማሪዎች ያካትታል።*

**የተማሪዎችን የባሕሪያት ሁኔታን በመኖሪያ ቤት ውስጥ መማር ጊዜ ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው የጣልቃገብነቶች (interventions) እና የእርዳታ አሰጣጦች ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?**

| የባሕሪ (Behavior) መግለጫ | ጣልቃገብነቶች (Interventions) እና እርዳታዎች |
|---|---|
| የምናባዊ (virtual) መማር አካባቢን (environment)፣ የሚያውክ ባሕሪ | ባሕሪ የመማሪያ አካባቢን የሚያውክ ሆኖ በሚገኝ ጊዜ፣ እነዚህም እንደ – ሐቀኝነት የጎደለው የቀለም ትምህርት፣ ተገቢ ያልሆነ ቋንቋን ወይም በእጅ/በሰውነት ምልክት ማሳየት፣ ከሚደረገው ንግግር (chat) ጋር ግንኙነት የሌለው ቁሶችን መለጠፍ (post ማድረግ) — አስተማሪው በቃላት ተማሪዎን ወደሌላ እንዲተላለፍ ሊያደርገው ይችላል፣ ከተማሪው ጋር በግል ስለሚያውከው ባሕሪ ለመነጋገር ይገናኛል፣ ከተማሪው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር ይመካከራል፣ ተማሪውን ስለራሱ ምልከታ እንዲያደርግ ይረዳሉ፣ ወይም ተጠያቂ የማድረግ ዕቅድን ይቀርፃሉ። |

| | |
|---|---|
| ጉዳት (harm) ለማድረስ ሙከራ የሚያደርግ ወይም የማስፈራራት ባሕሪ | የባሕሪ ችግር ለመፍጠር ሙከራ በሚደረግ ጊዜ ወይም ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራቶች በሚደረጉበት ጊዜ፣ እንደ ማንጓጠጥ/bullying (በ'chat' ውስጥ እያሉ)፣ የኦንላይን-ማንጓጠጥ/cyberbullying (በማህበራዊ ሚዲያ)፣ የጦር መሣሪያዎችን በማውጣት (የእውነተኛውን ወይም ተመሣሣይን)፣ በወሲባዊ ባሕሪ መሣተፍ፣ ከውንብድና ጋር ግንኙነት ወይም እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ወሲባዊ ክንውኖች (በወሲባዊ ምስል (pornographic) መሣሪያዎችን መጫን (post ማድረግ)፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን ፈቃድ ሳያገኙ መጠቀም፣ ዕፅ(ዖችን) ወይም የዕፅ መጠቀሚያ ዕቃዎችን (paraphernalia) መጠቀም፣ መሸጥ ወይም ማከፋፈል፤ የሚያካትት ሲሆን፤ አስተማሪዎች፣ የሚያውክ ባሕሪ ካለው ተማሪ ጋር ለብቻ ሊወያይ ይችላል፣ ከተማሪው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር ይማከራሉ፣ ተጠያቂ የማድረግ ዕቅድን ይቀርፃሉ፣ ወይም የግል የደህንነት ጥበቃ ዕቅድ ያወጣሉ። |

*ማስታወሻ፡ ተማሪው ጉዳተኝነት ካለው፣ የትምህርት ቤትዎ ቡድን፣ ከልዩ ትምህርት (special education) ጉዳይ አስፈጻሚ ጋር ወይም ከ504 አቀናባሪ ጋር ሊመካከሩ ይችላሉ።*

**የSEL የእርዳታ ክፍሎች[1] ምንድናቸው?**

DCPS፣ በድቅል (hybrid) አካባቢ ውስጥ፣ *በ'መኖሪያ ቤት ውስጥ በመማር ወቅትም ሆነ፤ ወይም በCare ክፍለጊዜዎቻችን ውስጥ'፤* ችግሮች ለገጠሟቸው እና ፈታኝ የሆነ ባሕሪ (behavior) ለሚያንፀባርቁ ተማሪዎች፣ የSEL የእርዳታ ስፍራን (Support Space) በመጠቀም ለተማሪዎች እርዳታን ለመስጠት ያቀርባል። ይህ ስፍራ (space)፣ በቲምስ (teams) አማካኝነት በተዘጋጀ የምናባዊ (virtual) አቀማመጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ በሚገኝ በአካል መገኛ አካባቢ ውስጥ ሊዘጋጅ ይችላል። የSEL የእርዳታ ስፍራ (Support Space)፤ ተማሪዎች ባሕሪያቸው ላይ ምልከታ እንዲያደርጉ፣ በSEL ስርዓተ ትምህርት እና ግንኙነትን ለማዳበር (Restorative Practices) ከአዋቂ እንክብካቤ ጋር በመሆን መሣተፍን እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች ከፍተኛ መጠኑ (maximum) 1-ሰዓት የሆነ ጊዜን በSEL እርዳታ ስፍራ (Support Space) ወይም በአንድ ክፍለጊዜ ጋር ተመጣጣኝ የሆነን ጊዜ ብቻ ያሳልፋሉ።

## B. ከትምህርት ቤት[2] መማር

*ይህ፤ በCARE ክፍል ውስጥም ሆነ፣ ወይም በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ክፍሎች ውስጥ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማር ፕሮግራሞችን ውስጥ የሚሣተፉ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያካትት ነው።*

### በCOVID-19 ወቅት፣ ስለ የግል መከላከያ መሣሪያዎች (personal protective equipment)፤ እንደ የፊት መሸፈኛዎች (masks) ባሉት ላይ፣ ስጋቶች አሉኝ። ስለግል መከላከያ መሣሪያዎች (personal protective equipment) የተሰጡ ሕጎችን የማያከብሩ ተማሪዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ መዘዞች ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

DCPS፣ የሁሉንም ትምህርት ቤት ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ፤ የዲሲ ጤና (DC Health)፣ የስቴቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE)ን፣ እና የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላትን (Centers for Disease Control and Prevention (CDC)ን፤ መመሪያን ይከተላል። ልዩ የሆነ ሁኔታዎችን ለመተግበር ካልሆነ በስተቀር፤ በዲሲ ጤና (DC Health) እና OSSE መመሪያዎች በተዘረዘረው መሠረት፣ ተማሪዎች እና ሠራተኞች የፊት መሸፈኛ (mask) እንዲያደርጉ፣ DCPS ያስገድዳል። ከዚህ በታች የሚገኙት እርምጃዎች፣ የፊት መሸፈኛዎች (masks) ለማድረግ እና በእድገት እክሎች ጋር ከግምት ውስጥ ማስገባቶች ውስጥ ለሚገጥሙ ችግሮች ትምህርት ቤቶች እንዴት በዚህ ዙሪያ ያሉ ጉዳዮችን መፍታት እንደሚችሉ፤ ለሚያስገድዱ መስፈርቶች ለማስተዋወቅ የተዘጋጁ ናቸው።

| ክስተቶች (Occurrence) | ቅድመ (Primary) (PreK – 2ተኛ) | አንደኛ ደረጃ (Elementary) (3ተኛ – 5ተኛ) | ሁለተኛ ደረጃ (Secondary) (6ተኛ – 12ተኛ) |
|---|---|---|---|
| 1 | ከCOVID-19 የደህንነት ጥበቃ ፕሮቶኮሎች ከማክበር ጋር (ማለትም፤ እንደ የፊት መሸፈኛዎችን (masks) ማድረግ፣ የማህበራዊ ርቀት መጠበቅ እና አካላዊ ንክኪ ማድረግ) የሚሄዱ የቃል መልዕክት ማስተላለፊያዎችን ተማሪዎች እንዲያገኙ ይደረጋል። | የደህንነት ጥበቃ መመሪያዎችን ለማጠናከር፣ ተማሪዎች የቃላት መልዕክት ማስተላለፊያዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል። | የደህንነት ጥበቃ ስነስርዓትን (etiquette) እና ተመራጭ የሆኑ ተሞክሮዎችን ለማጠናከር፣ ተማሪዎች የቃል መልዕክት ማስተላለፊያዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | ተማሪዎች፣ የደህንነት ጥበቃ ላይ የሚጠበቅባቸው ሁሉ ለማጠናከር፤ የ[COVID-19 ግንዛቤ ካርቶን ፊልሞችን (awareness cartoon)] ይመለከታሉ። | ተማሪዎች፣ የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅን ለምን መለማመድ እንዳለባቸው ለመረዳት፣ የCOVID-19 የደህንነት ጥበቃ [የመስሪያ ወረቀት (worksheet)] ላይ ይመደባሉ። | ተማሪዎች፣ *እንደ ኮሮናቫይረስ (coronavirus) ዓይነት ወረርሽኞች በከፍተኛ ደረጃ ለምን እንደሚስፋፉ፣ እና እንዴት "flatten the curve" ማድረግ እንደሚቻል"* የሚል [ጽሁፍን (article)] ለማንበብ መመደብ። ከዚያ በኋላ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ተማሪዎች እንዴት ደህንነትን ለማረጋገጥ መፍትሄዎችን መጠቀም እንደሚችሉ ለጽሁፉ ምላሽ ይሰጣሉ። |

1 Information revised.

2 Section B added to address mask wearing during learning at school.

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አስተማሪው፣ 1-ለ-1 የሆነ ሞዴል ያከናውኑ እና ተማሪው ጋር ውይይት ያደርጋሉ።<br><br>አስተማሪው፣ ወላጅን ያሳውቃል። | አስተማሪው፣ 1-ለ-1 የሆነ ሞዴል ያከናውኑ እና ተማሪው ጋር ውይይት ያደርጋሉ።<br><br>አስተማሪው፣ ወላጅን ያሳውቃል። | ተማሪዎች ስለጽሁፉ (article)፤ ከአስተማሪው ጋር ወይም ከሌላ አዋቂ ሠራተኛ ከሆነ ሰው ጋር ይወያያሉ። |
| 3 | ርዕሰ መምህሩ (Principal) ወይም ተወካዩ፤ ወላጅን ያነጋግራል።<br><br>አስተማሪው፣ 1-ለ-1 የሆነ ሞዴል ማከናወኑን ይቀጥል እና ተማሪው ጋር ውይይት ያደርጋሉ። | ርዕሰ መምህሩ (Principal) ወይም ተወካዩ፤ ወላጅን ያነጋግራል።<br><br>ተማሪዎች፣ የደህንነት ጥበቃ ላይ የሚጠበቅባቸው ሁሉ ለማጠናከር እና የCOVID-19 ስርጭትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል በሚደረግ ውይይት ላይ ለመካፈል፤ የCOVID-19 ግንዛቤ ቪዲዮን (COVID- 19 awareness video) ይመለከታሉ። | ተማሪዎች ከሚከተሉት አንዱን፡ COVID-19 teen survivor video፣ ወይም World Health Organization safety guidelines ቪዲዮን ይመለከታሉ።<br><br>ተማሪዎች፣ ባሕሪ የሚያስከትሉትን ውጤት፣ ከአዋቂ ሠራተኛ የሆነ ሰው ጋር እና ከወላጅ ጋር በስብሰባው ውስጥ ይወያያሉ። |
| 4 | ርዕሰ መምህሩ (Principal)፣ በCOVID-19 የደህንነት ጥበቃ ላይ የሚከናወኑትን ክንውኖችን እና የሚጠበቅባቸው ነገሮች ላይ ምልከታ ለማድረግ ወላጅን ያነጋግራል። | ርዕሰ መምህሩ (Principal)፣ የDCPS/CDC የጤና መመሪያዎችን ከተማሪ እና ወላጅ ጋር ምልከታ ያደርጋል።<br><br>ወላጆች፤ በCOVID-19 ላይ ከልጁ ወይም ከወጣቱ (teen) ጋር እንዴት መወያየት እንደሚችሉ፣ ቪዲዮ (video) እንዲመለከቱ ይበረታታሉ። | ርዕሰ መምህሩ (Principal)፣ ከተማሪ እና ከወላጅ ጋር በመሆን ኮንፈረንስን ይካፈላሉ፤ እንዲሁም፤ የCOVID-19 የደህንነት ጥበቃ ጥቆማዎች (tips) ቪዲዮ (video)ን፤ ቤተሰቦች እንዲመለከቱ ያበረታታል።<br><br>ተማሪ በባሕሪ ኮንትራክት ውስጥ ይመደባሉ። |

## C. ሁሉም የመማሪያ ሞዴሎች

### የተማሪዎችን ባሕሪ ላይ መፍትሄ ለመፈለግ፣ በጣልቃገብነቶች (interventions) እና በእርዳታዎች ላይ ሊሰጡ የሚችሉ ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

በተቻለ ከፍተኛ በሆነ መጠን፣ ትምህርት ቤቶች ለዕድሜ ተገቢ የሆኑ፣ አስተማሪ እና የሚያድስ ጣልቃገብነቶችን (interventions) እና እርዳታዎችን በመጠቀም፤ በመማሪያ አካባቢ ውስጥ የሚያውኩ ባሕሪያትን መፍትሄ ለመፈለግ የሚያግዙ፣ ነገር ግን በእጅጉ ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ጊዜን እንዲያጡ የማያደርጋቸው መሆን አለበት።

ሆኖም፤ የተማሪው ባሕሪ፣ ተማሪን ከክፍል(ሎቻቸው) ለተወሰነ የጊዜ መጠን እንዲወጡ የሚያስፈልጋቸው ሊሆን ይችላል። እገዳው (suspension) የሚተረጎመው፤ ተማሪውን ከመደበኛ የጊዜ ሰሌዳ የተሰጠው የቀለም ትምህርት ፕሮግራም፤ በስነ-ስርዓት መጣስ ምክንያት እንዲወጣ ማድረግ ማለት ነው።

እንደየ ባህሪያቸው፣ ተማሪዎች 'ከትምህርት ቤት ውጪ (out-of-school)' ሆነው እንዲቆዩ ሊደረጉ ይችሉ ይሆናል። ተማሪው፣ አንድ ጊዜ እገዳውን (suspension) ከጨረሰ፣ ተማሪው ወደክፍል መመለስ ይችላል። ተማሪው ከእገዳው (suspension) ከመመለሱ በፊት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ኮንፈራንስን እንዲካፈሉ፣ DCPS ሊጠይቃቸው አይችልም።

**ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳዎች (Out-of-School Suspensions)**

ከK-5ተኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ከአንድ (1) እስከ አምስት (5) ቀናት የሆኑ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊያገኙ ይችላሉ። ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን በሚያከናውኑበት ጊዜ፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ የለባቸውም:

- የትምህርት ቤት ህንፃው ውስጥ መግባት፣ ወይም በትምህርት ቤት ንብረት (property) ላይ መገኘት፤ ወይም
- በትምህርት ቤት ስፖንሰር (school-sponsored) በተደረጉ ዝግጅቶች ውስጥ ወይም ከትምህርት ውጪ የሚደረጉ (extracurricular) እንቅስቃሴዎች ውስጥ መካፈል።

ለማንኛውም ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን በማከናወን ላይ ለሚገኝ ተማሪ፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ የሚከተሉት ያደርጋል:

- በይፋዊው የDCPS የተቀረጸ ዘዴ (system of record) ውስጥ የእገዳው (suspension) በሰነድነት እንዲቀመጥ ማድረግ (የተማሪ ባህሪ መከታተያ/Student Behavior Tracker)
- ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) እንደ ፈቃድ ያገኘ (excused ሆኖ)፣ የተማሪውን ከትምህርት ገበታ የቀረበትን መመዝገብ፣
- በእገዳ (suspension) ላይ እያሉ፣ ተማሪዎች፣ የቀለም ትምህርት ቁሳቁሶችን እንዲያጠናቅቁ ማቅረብ፣ እና
- ወደትምህርት ቤት ተማሪዎች በሚመለሱ ጊዜ ያመለጧቸውን፣ ፈተናዎች (quizzes)፣ ልዩ ፕሮጀክቶችን፣ ወይም የመጨረሻ ፈተናዎችን እንደወሰዱ ማረጋገጥ።

## ከK-8ተኛ ክፍል ለሚገኝ ልጅ፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) መቼ ሊያገኝ እንደሚችል የመጠን ደረጃዎች አለው?

አዎን። በ2020-21 የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ፣ ከK-8 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ ከትምህርት ቤት ግቢ ውጪ የሚከናወን ባሕሪን ጨምሮ፤ ተማሪው አካላዊ ጉዳት ወይም ስሜታዊ ጭንቀት ሌላ ሰው ላይ፤ በፈቃደኝነት ካልፈጠሩ፣ ለመፍጠር ካልሞከሩ፣ ወይም ለመፍጠር ካላስፈራሩ በስተቀር፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊያገኝ አይችልም።

## ከ9-12 ክፍል ለሚገኝ ልጅ፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) መቼ ሊያገኝ እንደሚችል የመጠን ደረጃዎች አለው?

አዎን። በ2020-21 የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ፣ ከ9 እስከ 12ተኛ ውስጥ የሚገኝ ማንም ተማሪ፣ ተማሪው ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ካልሆኑ በስተቀር፤ በትምህርት ቤት ከ ½ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች ከ18 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ሲሆኑ፤ በ'ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)' ወይም በስነስርዓት ምክንያት አለመመዝገብ (disciplinary unenrollment) በሚከተሉት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል:

- የDCPS ወይም የትምህርት ቤት የአለባበስ ኮድ ወይም የደንብ ልብስ (uniform) ሕጎችን መጣስ፤
- ፈቃደኛ የሆነ እንቢተኝነት፣ ወይም

- ከትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እና በትምህርት ቤት የተዘጋጀ (school-sponsored) እንቅስቃሴ አካል ባልሆነ ቦታ የተፈጠረ ባሕሪ፣ ተማሪው የአካል ጉዳትን ወይም ስሜታዊ ጭንቀትን በሌላ ሰው ላይ፤ ሆን ብሎ ካልፈጠረ፣ ለመፍጠር ካልሞከረ፣ ወይም ማስፈራራትን ካላደረገ በስተቀር።

## ልጇ ሊያገኝ የሚችለው ከትምህርት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ቀናቶች ላይ የቁጥር መጠን አለው?

አዎን። ተማሪው በሚያገኘው ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ከ2018 የተማሪ በተመጣጣኝ ሁኔታ ትምህርት የማግኘት የተስተካከለ ድንጋጌ (Student Fair Access to School Amendment Act of 2018) ጋር ጎን ለጎን በመሆን፤ ተከታታይ እና የተጠራቀሙ የቀናት ቁጥር ላይ ገደቦች ይኖራሉ።

- ከK-5 ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ አምስት (5) ተከታታይ ቀናቶች የማይበልጥ፣ በአንድ የስነስርዓት ክስተት፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊሰጠው አይችልም።*
- ከ6-12 ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ አስር (10) ተከታታይ ቀናቶች የማይበልጥ፣ በአንድ የስነስርዓት ክስተት፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊሰጠው አይችልም።*

- ከK-12 ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ ሃያ (20) ተከታታይ ቀናቶች ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)፣ ለተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ፣ ለምን 20-ቀን ከሆነው ተገቢ የስነስርዓት እርምጃ የመጠን ገደብ በላይ የሆነበትን አማራጭ ምላሾች የሆኑበትን ምክንያቶች፤ ቻንስለሩ የጽሁፍ ማብራሪያ (justification) አቅርቦ ካላብራራ በስተቀር፤ ወይም የተማሪው ጠባይ የአስቸኳይ ጊዜ ማስወገድ እርምጃን እንዲፈጠር ካላደረገ፣ እና ቻንስለሩ ለተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ማስወገጃ የጽሁፍ ማብራሪያን (justification) ካልሆነ በስተቀር፣ እገዳውን አያገኙም።*

  *ማስታወሻ: ከዚህ በላይ ለተገለጹት መስፈርቶች የተለየ ሁኔታ የሚፈጥረው፣ ተማሪው የ'Gun-Free Schools Act' ድንጋጌን ከተላለፈ ነው። ይህ የፌደራል ሕግ በሚጠይቀው መሠረት፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የጦር መሣሪያን (firearm) ወደትምህርት ቤት ያመጣ ተማሪን ለማባረር፣ ወይም የጦር መሣሪያ በትምህርት ቤት ውስጥ የያዘ፣ ለሚማርበት ትምህርት ቤት ለአንድ ዓመት ያላነሰ ያግደዋል። ቻንስለሩ የማስወገዱን መስፈርቶች ማስተካከል ይችላሉ።*

## በእገዳው (suspension) ሂደት ላይ የልጅዎ መብቶች ምንድን ናቸው?

በሕጉ መሠረት፣ **ለፍትህ ሂደት** (**due process**) እርስዎ እና ልጅዎ መብት አላችሁ። ይህ ማለት፣ ስድስት (6) ቀን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እገዳ (suspension) በሚፈጠር ጊዜ፣ ስለተጠየቀው መወገድ ምክንያቶች ምን እንደሆነ ለማወቅ መብት ይኖርዎታል፤ በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ምልከታ ስለተደረገበት፣ ከተጠየቀው መወገድ ጋር ተያያዥነት ያለውን መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ማለት ነው። ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች ተጨማሪ የሆነ 'due process rights'ን፣ ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው ማግኘት ይችላሉ።

**የ'Due Process Rights' ለተማሪዎች በአጠቃላይ ትምህርት አሰጣጥ ላይ:**
በDCPS ውስጥ፣ ተማሪ በይፋዊ በሆነ ሁኔታ እገዳ (suspended) ሲደረግበት፣ ከዚህ በታች የሚገኙትን እርምጃዎችን መከተል አለበት። ተማሪው እገዳ (suspension) ሲያገኝ፣ ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- **ተማሪው አስተዳደራዊ ኮንፈራንስ የማግኘት ዕድል መስጠት**: ርዕሰ መምህሩ (principal) ወይም ወኪሎቻቸው፣ እገዳውን (suspension) ከማስፈጸማቸው በፊት፣ ከተማሪው ጋር ኮንፈረንስ ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን – የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ካልተፈጠሩ በስተቀር (ከዚህ በታች ይመልከቱ)፤ ይህ ከሆነ፣ እገዳው (suspension) ከተጀመረ በኋላ የጉዳዩ ኮንፈረንስ ሦስት (3) የትምህርት ቀናቶች ሳያልፍ እገዳው (suspension) ኮንፈረንስ መደረግ አለበት።
- **ከስተቱን መመልከት እና ተገቢ በሆነው የስነስርዓት ምላሽ ላይ ውሣኔ ማድረግ።**
- **ከእገዳው (suspension) ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በሙሉ፣ በሰነድነት መያዝ።**
- **ለወላጅ/ለአሳዳጊ፤ የቀረበውን የስነስርዓት እርምጃ ማስታወቂያን መላክ**: ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የቀረበውን እገዳ (suspension) እንዲያውቁት ለማድረግ በስልክ እንዲነገራቸው ይደረጋል። ማንኛውም እገዳ (suspension) በተደረገበት በ24 ሰዓታት ውስጥ፣ ለወላጅ/አሳዳጊ በአደራ ደብዳቤ (certified mail) ወይም በእጅ የተሠጠ፤ የጽሁፍ ማስታወቂያ መላክ አለበት። የፅሁፍ ማስታወቂያ በይፋዊ የDCPS የእገዳ (suspension) ማስታወቂያ የደብዳቤ አቀማመጥ ተዘጋጅቶ መሰጠት አለበት።
- **የትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ መፍጠር**: ከሁለት (2) ቀናት በላይ ለሆኑ እገዳዎች (suspensions)፣ ተማሪዎች የትምህርት አሰጣት ዕቅድ (educational plan) ለማግኘት ብቁ የሚያደርጋቸው እና በእገዳው (suspension) ወቅት ከአመለጧቸው ትምህርቶች ጋር ጎን ለጎን የሚሄዱ የ'work packet' ለማግኘት ብቁ ያደርጋቸዋል።
- **ተሰሚነት ማግኘት (Hearings)**: ለስድስት (6) ቀናት ወይም ከዚያ በላይ፣ እገዳ (suspended) የተደረገበት፣ ወይም የተባረረ ተማሪ፤ በገልተኛ የተሰሚነት ሹም (independent hearing officer) የተካሄደ የስነስርዓት ተሰሚነት የማግኘት መብት አለው።

**የአስኳይ ጊዜ (Emergency) በሚፈጥረው ሁኔታ የሚደረጉ እገዳዎች (Suspensions)**
የ"due process" ከመጠናቀቁ በፊት፣ ተማሪው ከመደበኛ የትምህርት አሰጣጥ ቀናቸው ውስጥ፣ ወዲያውኑ

የሚወገዱበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል ሲሆን፣ አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮች በትምህርት ቤት ውስጥ ለመፈጠሩ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ከሆነ መወገዱ ይከናወናል። ከአጠቃላይ ትምህርት አሰጣጡ፣ ተማሪው በአስቸኳይ ጊዜ መወገድ፣ ትምህርት ቤቱ ተማሪው አደገኛ የሆነ ማስፈራራት ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መፍጠሩን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት። የIEP ወይም የ504 ዕቅድ፣ ተማሪ የሆነ (ወይም ግምገማ የተደረገለት ከሆነ)፣ የተማሪው ባሕሪ ከሚከተሉት መስፈርቶች ቢያንስ ከአንዱ ጋር መዛመድ ይኖርበታል:

- ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የጦር መሣሪያ መያዝ፣
- ተማሪው ሆን ብሎ ሕገወጥ ዕፆችን መያዝ ወይም መጠቀም፤ ወይም ቁጥጥር ያለባቸውን ዕጾች በትምህርት ቤት ውስጥ እያለ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ በሚካሄድበት ቦታ መሸጥ፣ ወይም
- ተማሪው፣ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ፣ ወይም DCPS ስልጣን (jurisdiction) ውስጥ በሚካሄድ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ እያለ፤ አደገኛ የሆነ የአካል ጉዳት በሌላ ሰው ላይ ማድረስ።

**የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ወይም የ504 ዕቅድ፣ ላላቸው ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች፣ ማከናወኛ የሆነ የሂደት መብቶች**

የDCPS ሠራተኛ፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና የልጁ የIEP ቡድን ጋር ተዛማጅ የሆነ አባል፣ በተማሪው ፋይል ውስጥ የሚገኙትን ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን፤ የተማሪውን IEP ጨምሮ፣ ማንኛውንም የአስተማሪ ምልከታዎች፣ እና ሌላ ከወላጆች/አሳዳጊዎች በጥያቄ ላይ የቀረበው ባሕሪ ተፈጥሮ እንደነበር ውሳኔ በመስጠት፣ ወይም ቀጥተኛ የሆነ ጉልህ ግንኙነት እንደነበረው ለማወቅ፣ ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች፣ የልጁ ጉዳተኝነት፣ ወይም በጥያቄ የቀረበው ባሕሪ በDCPS የIEP አለማከናወን ምክንያት ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው፤ እነዚህን ሁሉ ይመለከታል። በአገልግሎት ላይ እጥረት ተደርጎ እንደነበር ከተወሰነ፣ DCPS ለእነዚህ እጥረቶች ወዲያውኑ መፍትሄ ይወስዳል። ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች በተቀመጠው፣ በክንውኖች የደህንነት ጥበቃ (procedural safeguards) ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ከፈለጉ፣ እባክዎን፣ https://dcps.dc.gov/specialeducation ይመልከቱ።

**እገዳዎች (suspensions) እንዴት ነው በትምህርት ገበታ መገኘት (attendance) ላይ ተፅዕኖ የሚያደርገው?**

በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳዎችን (in-school suspensions) በማሟላት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ገበታ እንደተገኙ ተደርገው ይቆጠራሉ። ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳዎች (out-of-school suspensions)፣ ፈቃድ የተሰጣቸው መቅረቶች (excused absences) ናቸው፤ በዚህ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳዎች (out-of-school suspensions) ምክንያት ለሚፈጠሩ መቅረቶች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ማመሳከሪያ ሰነዶችን ማስገባት አያስፈልጋቸውም።

## ስለልጄ እገዳ (suspension) ስጋቶች አሉኝ። ተጨማሪ መረጃዎች ከየት ማግኘት እችላለሁ፤ እንዲሁም በልጄ እገዳ (suspension) እንዴት ነው ይግባኝ ማለት የምችለው?

ለDCPS ስነስርዓት ፖሊሲዎች የሆኑት፣ የ2018 የተማሪ በተመጣጣኝ ሁኔታ ትምህርት የማግኘት የተስተካከለ ድንጋጌ (Student Fair Access to School Amendment Act of 2018) እና በቻፕተር 25 ስር፣ የዲሲ የማዘጋጃ ድንጋጌዎች (DC Municipal Regulations under Chapter 25) በሁሉቱም፤ መሠረት በማድረግ ነው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ማንኛውንም እገዳ (suspension) ይግባኝ ማለት መብት አላቸው። በይግባኙ ወቅት፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ማስረጃ ማቅረብ እና ምስክሮችም እንዲናገሩ መጠየቅ ይችላሉ። የይግባኝ ጥያቄ፣ በቃል ወይም በፅሁፍ መቅረብ ይችላል።

- ከK-5 ክፍሎች ውስጥ ላሉ ተማሪዎች፤ ከአንድ (1) እስከ ሦስት (3) ቀናት፤ ወይም ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ከአንድ (1) እስከ አምስት (5) ቀናት ያክል እገዳዎች (suspensions)፤ የይግባኝ ጥያቄው ተሰሚነት (hearing) የሚያገኘው በርዕሰ መምህሩ (principal) ሲሆን፤ እና የእገዳው (suspension) ማስታወቂያ በተቀበሉበት በሁለት (2) ቀናት ውስጥ ተሰሚነቱ ሊጠየቅ ይገባል።

- ከK-5ተኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ከአራት (4) እስከ አምስት (5) ቀናት ለሆኑ እገዳዎች (suspensions)፤ የይግባኝ ጥያቄው ተሰሚነት (hearing) የሚያገኘው በትምህርት አሰጣጥ የበላይ ተቆጣጣሪ (Instructional Superintendent) ይሆናል።
- ከ6-12ተኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፤ ከስድስት (6) እስከ አስር (10) ቀናት ለሆኑ እገዳዎች (suspensions)፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከገለልተኛ ተሰሚነት ሹም (independent hearing officer) በፊት፤ ለመጀመሪያው ተሰሚነት (hearing) ባለሙብት ይሆናሉ። ወላጅ/አሳዳጊ፣ ተሰሚነቱ (hearing)ን ተከትሎ በእገዳው (suspension) በተጣለው ላይ፣ ይግባኝ ማለት ከፈለጉ፣ በቻንስለሩ ተወካይ ይግባኙ ተሰሚነት የሚያገኝ እና የመጨረሻው የእገዳ (suspension) ውሳኔ ማስታወቂያ በተቀበሉት በአምስት (5) ቀናት ውስጥ፣ በወላጅ/አሳዳጊ ተሰሚነቱ መጠየቅ አለበት።

በሁሉም ጉዳዮች ውስጥ፣ ተማሪ እና/ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ስጋቶች ካሏቸው፣ ሁሉንም የDCPS ባለድርሻ አባላቶች (stakeholders)፣ ተመጣጣኝ እና ሚዛናዊ ተሞክሮዎችን ለሁሉ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በማመቻቸት ፈጣን የሆኑ የመፍትሄዎች ሂደት መደረጉን ለማረጋገጥ፤ የታማኝነት ቢሮ (Office of Integrity)ን ማነጋገር ይችላሉ። ከዚህ በላይ ከተፃፉት ሂደቶች በተጨማሪም፣ ወደ ታማኝነት ቢሮ (Office of Integrity) በስልክ ስጋቶችን ማመልከት እንደሚቻል ማስታወሳችን በጣም አስፈላጊ ነው። እባክዎን፣ ለእርዳታ በ(202) 939-4913 ወይም በDCPS.cio@k12.dc.gov ማነጋገር ይችላሉ።